# ለብሄራዊ ጤናና አመጋገብ ምርመራ ጥናት (NHANES) ንሃኔስ ተሳታፊ ለመሆን እንኳን አደረስዎት

## ንሃኔስ (NHANES) ምንድነው?

ንሃኔስ (NHANES) በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከሁሉም በላይ አርኪ ውጤትና የረጂም ጊዜ አገልግሎት ካላቸው ጥናቶች አንዱ ነው! በዚህ አገር ያለውን የጤና ሁኔታ በይበልጥ ለመረዳት ባለሙያዎች በሚያካሄዱት ጥናትና ምርመራ ወቅት፣ እርስዎም ተመርጠው ተሳታፊ በመሆንዎ፣ የጤና ምርመራ በነጻ ይደረግሎታል የምርመራውንም ውጤት በነጻ ያገኛሉ።

## እንዴት ነበር የተመረጥኩት?

እርስዎ ለምን እንደተመረጡ ሳይገርሞት አይቀርም። አመራረጡ የአሜሪካን የሕዝብ ቆጠራ ሥርዓት የተከተለውን ሂደት በመጠቀም ሲሆን፣ እርስዎም የተመረጡት በነሲብ ወይም በዘፈቀደ ሁኔታ ነው። ከተመረጡት ተሳታፊዎች አንዱ እነደመሆንዎ መጠን፣ በዚህም ሁኔታ እርስዎ የሚወክሉት እንደ እርስዎ ያሉ 65,000 ያህል ሰዎችን ነው። በምርምር ሥራችን ለመሳተፍ በገዛ ፍላጎታቸው የሚመጡ ሰዎችን ግን አንቀበልም። እርስዎ የሚሰጡን መረጃ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ሌላ ሰው ሊተካዎት አይችልም።

## ምንድነው ጥቅሙ?

በዚህ ፕሮግራም በመሳተፍዎ ስለሚያገኙት ጥቅም እንነጋገር። ከእርስዎ በኩል ያለ ምንም ወጪ፣ የጤና ምርመራ ይደረግሎታል፣ ውጤቱም እንዲሁ ይሰጥዎታል። የተለየ የጤና ምርመራ የሚደረግሎት፣ በእድሜዎ፣ በጾታዎና አሁን ባሉበት የጤና ሁኔታ ላይ በመንተራስ ነው። እነዚህም ውጤቶች፣ የራስዎን አጠቃላይ የጤና ሁኔታ በተመለከተ፣ አሁን ወደ ሃኪም ዘንድ ሲሄዱ ከሚያገኙት መረጃ ይበልጥ፣ ጠለቅ አድርገው ያሳዩዎታል። በዚህ ጥናት በመሳተፍ ስለሰጡት ጊዜ ክፍያ ያገኛሉ።

## እንዴት ነው የምሳተፈው?

መሳተፍ የሚችሉት እንደሚከተለው ነው። የእርስዎ ቤተሰብ ለጥናቱ ከተመረጠ፣ ቃለ መጠይቁን የሚያካሄደው ግለሰብ ቤትዎ ድረስ መጥቶ ያነጋግሮታል። ያ ግለሰብ እርስዎ ለዚህ ፕሮግራም ብቁ መሆንዎን ወይም አለመሆንዎን ይወስናል። ለፕሮግራሙ ብቁ ከሆኑ፣ ቃለ መጠይቅ አድራጊው፣ የእርስዎን የጤና ታሪክ በተመለከተ አንዳንድ ጥያቄ ይጠይቅዎታል።

ከዚያ በኋላ፣ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚሆን የጤና ምርመራ ቀጠሮ በእኛ ተንቀሳቃሽ የህክምና ሆስፒታል ይደረግሎታል።

የምሰጠው መረጃ በምሥጢር ይጠበቃል?

ንሃኔስ (NHANES) የርስዎን ምሥጢር እንደሚጠብቅ ቃል ይገባል። በቤት ውስጥ የሚካሄደው ቃለ ምልልስ ሆነ የሚደረግልዎ የጤና ምርመራ ሁሉ በአስተማማኝ ሁኔታ በምሥጢር ይያዛል። እርስዎ ካልተስማሙ በስተቀር፣ የእርስዎንም ሆነ የቤተሰብዎን ማንነት ለማንም በፍጹም አንነግርም።

ስለኔ የተሰበሰበው ዳታ/መረጃ እንዴት ነው ጥቅም ላይ የሚውለው?

በንሃኔስ (NHANES) የሚሰበሰቡ ዳታ/መረጃዎች ለብዙ አስፈላጊ ለሆኑ አገራዊ የጤና ጉዳዮች፣ ጥቅም ላይ ይውላሉ። ለምሳሌ በሃኪም ቢሮዎች ውስጥ የሚሰቀለውን የልጆችን እድገትና ክብደት የሚያሳየውን ሰንጠረዥ ልብ ሳይሉ አልቀሩም። የአገሪቷን የጤና አዝማሚያ ለመጠቆም፣ የንሃኔስ (NHANES)ዳታ/መረጃ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህም ውፍረትን፣ የስኳር በሽታንና የደም ግፊትን ያካትታል።

የእኛን የጥናት ምርምር በተመለከተ ወይም የበለጠ መረጃ ከፈለጉ በጻፍንልዎ ደብዳቤ መግቢያው ላይ የሰፈረውንና በነጻ የሚደወለውን ስልክ ደውለው ያግኙን። የስልኩ ቁጥር 1-800-452-6115 ነው። በምሥራቅ ዩናይትድ ስቴትስ ሰዓት አቆጣጠር ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጠዋቱ 8:30 እስከ ምሽቱ 6:00 ከደወሉልን እንገኛለን።